# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የሕንጻ ፈንድ ማሰባሰብ ፕሮግራም

ለሕንጻ ግዢ ለመስጠት ቃል የገባነውን ገንዘብ **በNovember 19 ወይንም እስከ አመቱ መጨረሻ** (ወይንም ቃል በገባነው መሰረት) እንድንሰጥ እናበረታታችኋለን። ፎርሙን ሞልታችሁ ያልመለሳችሁ ወገኖች ደግም አባካችሁ ሞልታችሁ ለዲያቆናት ስጡልን። የህንጻ ኮሚቴ አስተባባሪዎች። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

### የጸሎት አርዕስት

በፊታችን ላለው የሽማግሌዎች ምርጫ እየጸለይን እንድቆይ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች።

### የጌታ እራት

በሚቀጥለው ሳምንት የጌታ እራት ፕሮግራም ስለሚኖረን ሁላችንም ስለዚህ ፕሮግራም እየጸለይን እንድንቆይ በጌታ ፍቅር እንጠይቃልን።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ **Yeec.org App** ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| | | |
|---|---|---|
| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም።" (ኤር. 29፡11)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**November 12, 2017** | **ሕዳር 3፤ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................ | ሕህት ሒሩት ደሳለኝ |
| አምልኮ...................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም አያሌው አስፋው |
| ቃል ......................... | ወንድም ሰለሞን ወመገ |
| ማጠቃለያ ................ | ፕሮግራም መሪ |

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

"የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።"
(ሮሜ. 12፡ 2)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመገ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ጸሎት አስተምረን -- መንግስትህ ትምጣ —ፈቃድ (ክፍል አስር)

*"እርሱም በአንድ ስፍራ ይጸልይ ነበር፥ በጨረሰም ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፡- ጌታ ሆይ... እንጸልይ ዘንድ አስተምረን አለው። አላቸውም፡- ስትጸልዩ እንዲህ በሉ፡- በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ... <u>ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን</u>..." (ሉቃ. 11፡1-2)*

ጌታ ባስተማረው ጸሎት ውስጥ የምንጸልየው ሌላው ጉዳይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈለግ ነው። ብዙ ጊዜ እንደሚባለው ጸሎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናስቀይርበት ሳይሆን እኛ የእርሱን ፍቃድ አውቀን ወደ ፈቃዱ የምንገባበት ነው። በሰማይ የእግዚአብሔር ፈቃድ በፍጹም ትከናወናለች። በምድር ፈቃዱ ትፈጸም ዘንድ ግን የቅዱሳን ጸሎትና ምልጃ ያስፈጋል።

የእግዚአብሔር ሰው ዶክተር ማይልስ ሞንሮ ሲናገር "ጸሎት እግዚአብሔር በምድር እንዲሰራ የምንፈቅድበት መንገድ" ነው ብሷል። ለዚህ ምክንያቱ እግዚአብሔር **በቃሉ** ምድርን የመግዛትን ስልጣን የሰጠው ለሰው ስለሆነ ነው። (ዘፍ. 1፡27) ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር ቃሉን የሚሽር (የሚጻረር) አምላክ ስላልሆነ ለሰው በሰጠው የማስተዳደር ስልጣን ያለ ሰው ፍቃድ አይገባም። ስለሆነም የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር እንዲሆን ስንጠይቅ እርሱ በማንኛውም ጉዳያችን ጣልቃ ገብቶ ፍጹም የሆነው ፈቃዱ ይከናወን ዘንድ ነው። ስለዚህ ነው እግዚአብሔር ምድርን በተመለከተ ከፍተኛ ስልጣን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው። እናስታውስ፡- ቃሉ እንደሚለን በምድር የምናስረው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምንፈታው ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል። (ማቴ. 18፡18) ነገር ግን በምድር የእግዚአብሔር ፈቃድ ይከናወን ዘንድ ማለትም በምድር የምናስረው በሰማይ የታሰረውን፤ እንዲሁም በምድር የምንፈታው በሰማይ የተፈታውን እንዲሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅና መፈለግ አለብን።

ቃሉ እንደሚያስተምረን የእግዚአብሔር ፍቃድ በጎ፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም ነው። (ሮሜ. 12፡2) የእግዚአብሔር ፍቃድ መልካም ነው። በፈቃዳችን ለፍቃዱ ስናድር በጎነቱ በሕይወታችን ይገለጣል። እንደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፈቃዱ ስንጨክን ለጊዜው ምንም እንኳ ጽዋው መራራ ቢሆንም በፈቃዱ በሄድነው መስመር መጨረሻ በጎነቱ ታገኘናለች። ለኛ ደስታችን ያለው በፍቃዱ ውስጥ ነው። በእርግጥ አለ እግዚአብሔር ፍቃድ የበላ ደስ ብሎትም ተድላን የቀመሰ የለም። ፈቃዱ ፍጹም ነው። የእግዚአብሔር ፍቃድ በሕይወታችን ሲከናወን ያን ግዜ ለተፈጠርንበት አላማ እየኖርን ነው።

ወገኖቼ፡- እግዚአብሔር ለኛ መልካም ነው። ለኛ ያለው ሃሳብ በጎ ነው። ለኛ ያለው ሃሳብ ፍጻሜና ተስፋ ያለው ነው። ፍቃዱን መፈለግና በፍቃዱ ውስጥ መግባት ትልቅ በረከት ነው። አባታችን ሆይ ፍቃድህ በሕይወታችን ትሁን። አሜን!